# መመሪያ ቁጥር 1033/2017

# የቅባት እህሎች እና የጥራጥሬ ምርቶች የቀጥታ ግብይትን ለመወሰን የወጣ መመሪያ (ማሻሻያ) መመሪያ

የቅባት እህሎች እና የጥራጥሬ ምርቶች የቀጥታ ግብይትን ለመወሰን የወጣውን መመሪያ ቁጥር 1026/2017 ማሻሻል በማስፈለጉ፤

የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር በአስፈጻሚ አካላት ሥልጣንና ተግባር መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 1263/2014 አንቀጽ 19 (4) በተሰጠው ሥልጣን መሰረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

1. <u>አጭር ርዕስ</u>

   ይህ መመሪያ "የቅባት እህሎች እና የጥራጥሬ ምርቶች የቀጥታ ግብይት መመሪያ (ማሻሻያ) መመሪያ ቁጥር 1033/2017" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2..<u>ማሻሻያ</u>

የቅባት እህሎች እና የጥራጥሬ ምርቶች የቀጥታ ግብይትን ለመወሰን የወጣው መመሪያ ቁጥር 1026/2017 እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡፡

1. የመመሪያው አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ (1) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (1) ተተክቷል፡፡

   "1/ማንኛውም አቅራቢ እና ላኪ በዚህ መመሪያ መሰረት በሚፈጠር የግብይት ትስስር የቅባት እህሎች እና የጥራጥሬ ምርቶች የቀጥታ ግብይት ማካሄድ ይችላል፡፡"

2. የመመሪያው አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ (3) ተሰርዟል፡፡
3. የመመሪያው አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ (2) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (2) ተተክቷል፡፡

   "2/ የቀጥታ ግብይት ትስስር ለገባለት ላኪ ማስረከብ ያለበትን ምርት አቅርቦ ሳያጠናቅቅ ለሌላ ገዥ ሽያጭ ያለመፈጸም፤"

4. የመመሪያው አንቀጽ 15 ንዑስ አንቀጽ (2) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (2) ተተክቷል፡፡

"2/ የቀጥታ ግብይት ትስስር ለገባለት ላኪ ማስረከብ ያለበትን ምርት አቅርቦ ሳያጠናቅቅ ለሌላ ገዥ ሽያጭ መፈጸም፤"

3. <u>የመሸጋገሪያ ድንጋጌ</u>

ይህ መመሪያ ከመውጣቱ በፊት የተደረገ ውል የተፈጻሚነት ሁኔታ በተዋዋይ ወገኖች ስምምነት የሚወሰን ይሆናል፡፡ ሆኖም ተዋዋይ ወገኖች ካልተስማሙ መብትና ግዴታቸዉ በዉሉ መሰረት ይሆናል፡፡

4. <u>መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ መመሪያ በፍትህ ሚኒስቴር ከተመዘገበበት እና በሚንስቴሩ ይፋዊ ድረ-ገጽ ላይ ከተጫነበት ቀን ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ታህሳስ 8 ቀን 2017 ዓ.ም**

**ካሳሁን ጎፌ ባለሚ (ፒ.ኤች.ዲ)**

**የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር ሚኒስትር**